ግንቦት 7 ቀን 2002 ዓ.ም.

# ግልጽ ደብዳቤ

1. ለአቶ ማለስ ዜናዊ እና ለወያኔ ድርጅት፣

2. ለአቡነ ጳውሎስ ፣

3. በየጊዜው ከሚፍሰው ነፋስ ጋር ለምትነፍሱ ብልጣብልጥ ሆድ አደሮች፣

4. ለተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ድርጅቶች፣

5. ለማለዮ ለባሹ ሠራዊት፣

6. ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ፣

ከሁሉ በማስቀደም በየአቅጣጫው ሁላችሁንም ከሚያጋጥማችሁ ስህተቶች እየተገታችሁ ወደ ቁምነገር በመማለስ በጎ በጎውን እንዲያሳስባቹሁ እመኝላች|ለሁ፡፡ እውነት እንደሬት የምትመር እንደ ኮሶ የምታንገፍግፍ ስለሆነች ብዙ ጊዜ አቅራቢያዎቿን ትሰዋለች፡፡

እግዚአብሔር እድሜ ማስተዋል ሰጥቶኝ ከዛሬ 50 አመት በፊት ጀምሮ አስከዛሬ ድረስ ባለሁብት ዘመን ሁሉ ባለማቋረጥ የሀገሬ የኢትዮጵያ ጉዳይ ሲያስጋኝ፣ ሲያሳስበኝና፣ ሲያስቃየኝም በመኖሩ እውነት ነው ብዬ ካመነከብትና መሆን ይገባዋል ብዬ ካሰብኩብት ጥቂቱን ልገልጽላችሁ እወዳለሁ፡፡

የዚህ አይነቱን ገለጻና ማስጠንቀቂያ ስሰጥ ይህ የመጀመሪያዬ ሳይሆን ለምሳሌ አንደኛ በጥር ወር 1962 ዓ.ም. በምዕራብ ጀርመን በትምህርት ላይ በነበርኩብት ጊዜ ከሶስት [1]ደኞቼ ጋር በመመካከር ኢትዮጵያ ሊደርስባት የሚችለውን ጥፋት በማምገምና ለጥፋት የሚያደርሱትን ምክንያቶች በማዘርዘር እንዲሁም ከጥፋቱ የሚያድኑ ዘዴዎችን በማጠቆም 12 ገጽ ጽሑፍ አዘጋጅተን ስማችንን ሳንፈርም ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ልዩ ካቢኔና ለሚኒስትሮቻቸው በፓስታ ልከን ነበር፡፡ ዘዴ ብለን ከጠቆምነው ዋና ዋናው 1ኛ/ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲቋቋሙ፡ 2ኛ/ በፓርቲዎች ነጻ ወድድር የሚያሸንፈው ፓርቲ በሚመርጠው ጠቅላይ ሚኒስትር የሚመራ መንግሥት እንዲቋቋም፡ 3ኛ/ የሚኒስቴር ማሥሪያ ቤት ተቋቁሞለት በማዘገም ላይ የቆዬው የሜት ይዞታ ድልድል ባስቸኳይ ተግባራዊ እንዲሆን የሚል ነበር /እዚህ ላይ እግረ መንገዴን ስለባለሜቶች ለመጥቀስ ብዙ መትንተን አስፈላጊ በመሆኑ ባለ50፣ ባለ100 ጋሻ የነበሩት ራስ ደጃዝማቾች ጥንት ሜቱን የያዙት ለሠራዊቶቻቸው መመጊያ ሲሆን የነፍጠኛው ሠራዊት ቀርቶ በደመወዝ የሚተዳደር ወታደር መቀጠር ከጀመረ በ|ላም ቀድመው የተመሩት ባለርእስቶች አልቀው በወራሾች ስለተበታተነ የተጋነነ ጋሻ ሜት የነበራቸው ብዙ አልነበሩም፡ /እስከ ለወጡ ጊዜ ድረስ ብቻውን መቶ ጋሻ ሜት የነበረው ሰው ቢኖር የአሁኑ ፕሬዚዳንት መቶ አለቃ ግርማ ወልደጊዮርጊስ ብቻ ለመሆናቸው ድሮና ዘንድሮ የተባለው መጽሐፋቸው ያስረዳል/ 4ኛ/ ጃንሆይም የሕዝብ አባት በመሆን የሀገሪቱን አንድነት እንዲያስከብሩ ወዘተ የሚል ሲሆን ይህ ሳይደረግ አንድ አደጋ ቢመጣ ሌላ የተደራጀና የተዘጋጀ ኃይል ባለመኖሩ ወታደር ለጊዜው ሥልጣኑን ለማያዝ ይችላል በማለት በወታደር ሥልጣን የሚደርሰውን አደጋ ሁሉ ዘርዝረን ነበር/ የሀሳቡ አቅራቢዎች ወታደራዊ መኮንኖች ስንሆን ሀሳቡ በተግባር ሳይውል ቀርቶ ከሀሳቡ አቅራቢዎች አንዱ ሻለቃ ታዬ ባለከር በደርግ ዘመን ጄኔራል ተብሎ የኤርትራ ፓሊስ አዛዥ በነበረበት ዘመን መንግሥቱ ኃይለማርያምን ለመገልበጥ ተባብረሀል በማል የደርግ ዘመን ሰው በላ ወታደሮች ሁለት አይኑን አወጥተው ከጅፕ መኪና ጋር በገመድ አስረው በአስመራ ጎዳና ላይ እራቃኑን እየጎተቱ አሰቃይተው ገድለውታል፡፡ ሻለቃ አበራ ተፈራ /ኮሎኔል/ በዘመነ ወያኔ በስደት ላይ እያለ ሞተ፡፡ ሻምበል ፈቃዱ ዋኬኔ /[1]ድ / አዲስ አበባ በሕይወት መኖሩን ሰምቻለሁ፡፡

የቀ.ኃ.ሥላሴ መንግሥት አስከፊወን የባሪያ ሥርአት በማስረዝ የሰው ልጅ የእኩልነት አዋጅን ያወጀ፣ ኢትዮጵያን የአለም ማህበር አባል ያደረገ፣ የኢትዮጵያን አንድነት ያስከበረ፣ በጣሊያን ኮሎኒ ስር ወድቃ የነበረችወን የባህረ ነጋሽን አወራጃን ነጻ በማውጣት የኢትዮጵያን ባህር በሮች አስሜልሶ የነበረ፣ ከአንድ ትምህርት ቤት ተነስቶ በሺህ የሚቆጠሩ ትምህርት ቤቶች ከፍቶ ሕዝብን በስፋት በማስተማር የታወቀ፣ የአፍሪካን አንድነት ድርጅት የማስረተ ወዘተ... የማሳሰሉትን የእደገት ማስረት ጥሎ የነበረው መንግሥት በሜጨሻ ግን ምክራችንን ባለማዳመጥ ሰው በላወን የደርግ ሥርአት ተክቶ በከፋ ሁኔታ ወደቀ፡፡

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ለመወደቅ 6 ወር ሲቀረው ሕዝቡ በተለይም ተማሪ፣አስተማሪና የመንግሥትና የፋብሪካ ሰራተኛ ሁሉ በየአቅጣጫው አመጽ ስለሸተተው የርስበርስ ጦርነት ተነስቶ ሕዝብ እንዳይተላለቅና አገሪቱ እንዳትከፋፈል በማለት በስጋት ላይ የነበሩ ሶስት መኮንኖችና ሶስት ሲቪሎች፣ ከፖሊስ አንድ፣ ከጦር ሰራዊት አንድ፣ ከክብር ዘበኛ አንድ በጠቅላላው የስድስት ግለሰቦች ኮሚቴ የካቲት 15 ቀን 1966 ዓ.ም. በዩኒቨርሲቲ ቅጥር ጊቢ ወስጥ በሚገኝ ቢሮ በምስጢር ተሰበሰበ፡፡ ከዚያም ኮሚቴው ሕዝቡ ተማሪወና ወታደሩ ሳይከፋፈል ባንድነት ተባብሮ ሕዝባዊ መንግሥት ለማቋቋም እንዲችል የሚቀስቅስ ጽሑፍ አዘጋጅቶ ከኮሚቴ አባሎች አንዱ ኮሎኔል ይገዙ ይመኔ በአርሚ አቬዬሽን ሄሊኮፕተር ጽሁፋን በየጦር ሰፈሩና በዩኒቬሲቲ ቅጥር ግቢ ጫምር በተነው፡ የጽሑፋን ይዘትና የወታደሩን መተባበር ከተማለከቱ በ|ላ ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ በሶስተኛው ቀን ከነካቢኔአቸው በፈቃዳቸው ከሥራቸው ለቀቁ፡፡

ለአህያ ማር አይጥማት እንደተባለው ሆኖ ነው እንጅ እነ አቶ አክሊሉ የፈጸሙት ማስዋዕትነት ከፍተኛ የዲሞክራሲ ብልጫታ ነበረ፣ አነድ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ወስጥ አቶ እንዳልካቸው መኮንን ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው በሞኸም አዲስ መንግሥት አቋቋሙ፡ በምሥጢር የተቋቋመው ኮሚቴ አላማው አቶ እንዳልካቸወን ሞኸም ባይሆንም የፓለቲካ ፓርቲዎች ተቋቁመው እስኪደራጁና በፓርቲው የተመረጠ ጠቅላይ ሚኒስትር እስከሚኾም ጊዜ ለማገኘት የኮሚቴወን አባላት ቁጥር ወደ 12 ከፍ በማድረግና በየቦታው ተወካዮችን በመመደብ እንቅስቃሴወን በመቀጠል ላይ እያለ አቶ እንዳልካቸው ሥልጣናቸወን አጠናክረው ለመቆዬት ባላቸው ምኞት የአየር ወለድ ጦር አዛዥ በነበሩት በኮሎኔል አለምዘወድ በማጠቀም በፈቃዳቸው ከሥራቸው የተሰናበቱትን አቶ አክሊሉ ኃብተወልድን የቀሩትንም ባለሥልጣኖች አሳሰሩ፣ቀጥሎም የለወጡን አንቀሳቃሽ ኮሚቴ ለማስመታት ሲዘጋጁ ኮሚቴው በወሰደው አጸፋ እርምጃ የአቶ እንዳልካቸው ቀኝ እጅ የሆኑት ኮሎኔል ዓለም ዘወድ ተይዘው ሊታሰሩ ሲሉ አምልጠው ወደትወልድ ሥፍራቸው ሄደው ተደበቁ፡፡

ሆኖም ጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው በኮሎኔል ዓለም ዘወድ በኩል ያወቁትን ሻለቃ አጥናፉ አባተን ማጠቀሚያ ለማድረግ አስበው ከአጥናፉና ከጥቂት 50 አለቆች ጋር ተገናኝተው በእድሜ በሀሳብ ብዛት ተዳከመው ወደነበሩት ንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ በማቅረብ ግንቦት 22 ቀን 1966 ዓ.ም. ከሻለቃ ጀምሮ ወደታች ባለው ማዕረግ የሚሟሉ የወታደራዊ ኮሚቴ/ደርግ/ እንዲቋቋም አደረጉ፡፡ አቶ እንዳልካቸው ዘዴ የማሳላቸው በማዕረግም ሆነ በዕወቀት አነስተኛ የሆነው ቡድን ትእዛዜን ተቀብሎ መንግሥቴን ያጸናልኛል የለወጡን እንቅስቃሴ በምስጢር የሚሟሉወንም ኮሚቴ ያጠፉልኛል በማለት ነበረ፡፡

በድንቁርናው የተመረጠው ደርግ ሲቋቋም ተምረናል አወቀናል ሶሻሊሰቶች ነን ኮሚኒስቶች ነን አገሪቱን እኛ መምራት አለብን ከሚለው ወገንም ከፊሉ ደርግን መሳሪያ አድርገን ከተጠቀምን በ|ላ ሥልጣኑን እንይዛለን ብለው በማሰብ የደርግ ተባባሪዎች ሆኑ፡፡ ደርግ በተቋቋመ ሰሞን ቀደም ሲል አቶ እንዳልካቸው ካሳሰሩዋቸው ወስጥ የተረፉትን ሚኒስትሮችና ባለሥላጣኖች ሲያስር ሰንብተ ቆየት ብሎም

ደባ እራሱን ስለት ድጉሱን እንደተባለው አቶ እንዳልካቸውን አሰራቸው፡፡ በየካቲቱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የርስ በርስ ጦርነት እንዳይነስ ማገዱን ካስተካከሉት ስድስት የኮሚቴ አባላት መካከል ሁለቱ ኮሎኔል ይገዙ ይሜና ሻምበል ደምሴ ሽፈራው ከ60ዎቹ ባለሥልጣኖች ጋር ተረሸኑ፡፡ ሁለቱ ሲቪሎችም በተከታታይ ተገደሉ፡፡ እኔም አገሩን ለቅቄ ወጣሁ፡፡

ከአገር ከወጣሁም በ|ላ ለደርግ፣ለማለዮ ለባሹ ሰራዊትና ለሕዝቡ ኢትዮጵያን ለማዳን መፍትሔ ይሆናል ብዬ ያመንኩበትን ኃሳብ ሁሉ በሬዲዮ፣ በካሴትና በጽሐፍ መልክት ሳስተላልፍ ቆይቼ ነበር፣ ካስተላለፍኩት መልዕክት ወስጥ አንዱን አሜሪካ ዋሽንግተን ሲያትል በስደት ነዋሪ የሆኑት ዶክት አሉላ ዋሴ ስላገኙት «ይህም ያልፋል» በሚል አርእስት ባሳተሙት መጽሐፋቸው ላይ «መግቢያ» በሚል ክፍል ከገጽ 27 እስከ ገጽ 37 ለመንግሥቱ ኃይለሚርያም ያስተላለፍኩትን መልዕክት ስላሰፈሩት ከጽሁፉ ሁለትን ገጽ ከዚህ ጋር አያይዤዋለሁ፡፡

10-06-1990

ገጽ-27

ለጓድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም
የኢትዮጵያ የጭሌት መንግሥት ፕሬዚዴንት፣

ገጽ 36

የሚከተሉትን ምክሮች ብትከተል መልካም ይሆናል።

1ኛ. በኢትዮጵያ ስም የምለምንህ ጠሉኝ፣ ተቃወሙኝ በማለት ሕዝቡን መግደል እንድታቆም፣

2ኛ. የኢትዮጵያ መከራ ለባሽ ሠራዊት እንዳይበታተን ለማድረግ ከየክፍሉ ጦሩ ከሕዝብ ደም ያልተቃቡ በችሎታና በአገር ፍቅር የታወቁ በአስተሳሰብ የበሰሉ አንዳንድ መኰንኖችን በማስመረጥ፣

3ኛ. ከአገር ሽማግሌዎች፣ ከገበሬው ማሕበር፣ ከሠራተኛው ማሕበር፣ ከዩኒቨ ርሲቲ ምሁራን፣ ከመምህራንና ከፖሊስ ሠራዊት በጠቅካካው ከእምሳ ያልበከሉ የጊዜያዊ መንግሥት መገናኛ ኮሚቴ አስመርጠህ ኮሚቴው በኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ውጪ ከሚገኙ ከፖለቲካና ከትግል ድርጅቶች ጋር ተወያይቶ የመሸጋገሪያ መንግሥት በማቋቋምና ከዚያም በሕዝብ ድምጽ ብልጫ የሚመረጥ ሕዝባዊ መን ግሥት የሚቋቋምበትን ስርአት እንዲመ ሰርት፣

7837

4ኛ. ጃንሜዳ ወይም መስቀል አደባባይ
ሕዝቡን ሰብስበህ ከወታደሩና ከሕዝቡ
የተውጣጣውን ኮሚቴ ለሕዝቡ አስ
ውቀህ አንተ በድንቁርናህ ተሳስተህ
በአገርህ ላይ ያደረስከውን ጥፋትና
በደል ለሕዝብ ገልጸህ በማስረዳት ቢቻል
ቢቻል በሰውነትህ ላይ ነዳጅ አርከፍክ
ፈህ በሕዝብ መካከል ራስህን ብትቃጥል
ወይም ራስህን ለማቃጠል ድፍረት
ከሌለህ-ከጎደለህ በመሣሪያ ራስህን
ብትገድል እንደኛ ለአገሩ ሲል ራሱን
ገዳገገደ የገደለ መሪ በመባል ታሪክ ታገ
ኛለህ፣ ሁለተኛ ያስመረጥከው ኮሚቴ
የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማገናኘት የተሻለ
ተቀባይነት ይኖረዋል።

እኔ እንኳን በህይወቴ ዘመን በአገሬ
ሆኘ በግል ሰዎች ላይ የፈጸምኩት በደል
ባይኖርብኝም ኢትዮጵያን ለማዳን ራሴን
ማቃጠል የሚበጅ ቢሆን ኖሮ ያለቅሬ፡
በፈጸምኩት ነበር። ያንተ መቃጠል ግን
ለኢትዮጵያ ደህንነት እንደሚረዳ አያ
ጠራጥርም።

----- አገርህን ከመጨረስ ሞሉት አድ
ነህ በክብር ራስህን ብትገድል ትከበራለህ።

ከፓሪስ
ፈረንሳ።

ታጋይ. ኮሎኔል: አስራት. ቦጋለ

መንግሥቱ ግን በምክሬ ተጠቅሞ ኢትዮጵያን አደኖ ታሪክ ሰርቶ ከማጮት ይልቅ «አንድ ጥይትና አንድ ሰው እስኪቀር» «ኢትዮጵያ ወይም ሞት» በማለት እንደአንበሳ ሲፎክር መኖሩን ዘንግቶ ኢትዮጵያን የጠላት ቅጥረኛ ለሆኑት ለወያኔና ለሻቢያ አስረክቦ እንደወሻ ጅራቱን ሸጉቦ ወደ ዝምባቤ ሸሜጠጡ፡፡

«ከቆራጡ መሪያችን ጋር ወደፊት» በማለት በስርአት አልበኝነትና በጋጠወጥነት የተደራጀወም ግማሽ ሚሊዮን ማለዮ ለባሽ ሰራዊትና እንዲሁም ኢሰፓ የተሰኘው ፓርቲ አባላት ሚኒስትሮች፣አምባሳደሮች፣ጄኔራል፣ኮሎኔል፣ሻለቃ ሻምበል እየተባባለ ደረቱን ነፍቶ ከመንግሥቱ ጋት አብሮ ሲፎክር የነበረ ሁሉ ወህ እንደገባች አይጥ ኮምሽሾ መካሪያወን ከጫከ ለማጡ ሽፍቶች እያስረከበና እየተለቀመ በየወህኒ ቤት ከማጎር በስተቀር ያ የገዛ አለቆቹን ጫምር አይን ያጠፉና አንገት ሲቆርጥ የነበረ ጨኸኝ የመንግሥቱ ኃይለሚርያም ታማኝ ወታደር መቶ ሁለት መቶ እንኳን ሆኖ በመተባበር መካሪያዬን አላስረክብም እጄን አልሰጥም ብሎ ያንገራገረ አንድ ቡድን እንኳን ባለማኘቱ ኢትዮጵያ በወታደሮቿ አፍራለች፡፡

ላለፉት 50 አመታት ለትግልና ለትዝብት አስቀምጦኝ ሲወጡ፤ ሲወርዱ፣ ሲፎክሩና ሲዋረዱ ማየትን እንደ እድል ስለቆጠረልኝ እንዲህ ብዬ ነበር የሚለወን አልፌ ዛሬም የሚከተለወን ለማለት በሥልጣን ላይ ለሚገኘው በአቶ ማለስ ዜናዊ ለሚመራው የወያኔ መንግሥት የሚከተለወን አሳስባለሁ፡፡

**<u>አንደኛ/</u>**አቶ ማለስ ! በኢትዮጵያ በነጻ የፖለቲካ ወድድር የሚመራ ምርጫ ከተደረገ እኔም አንተም ማን እንደሚያሸንፍ እናወቃለን፡፡ ግን በአሁኑ ሁኔታ አንተና ወያኔ ታሸንፉላችሁ ብዬ ተወራርጃለሁ፡ ባለፈው 1997 ዓ.ም. በተደረገው ምርጫ ምርጫው ከመደረጉ ቀደም ብሎ አስቸኳይ ሜልከት በሚል ማሻ ዞሮ!ዞሮ! ምርጫው ዜሮ 0 በሚል አርእስት አንዲት አነስተኛ መጽሐፍ ጽፌ በበተንኩ ጊዜ ከናንተ ይልቅ ተቃዋሚዎቹ ተወዳዳሪዎች ምን ያህል ጥላቻ እንዳሳደሩብኝና አንዳንዶቹም እንደዘለፉኝ አስታውሳለሁ፡ ግምቴ ትክክል መሆኑን የተገነዘቡት የአሸናፊዎቹ አሸናፊነት ተገልብጦ ተሸናፊው ባሸናፊነት ሥልጣኑን አጠናክሮ በማያዝ አሸናፊዎችን ወደወህኒ ከላካቸው በ|ላ ነው፡ አቶ ማለስ እንግዲህ አሁን ከመቶ ሰማንያው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆዱ ተርቦ እያከከ በችግርና በብስጭት ኖሩሉ ወድቆ በደነዘዘበት ሰዓት አንተና ፓርቲህ፣ 1.ኤርትራን በማስገንጠልን ኢትዮጵያን ወደብ አልባ በማድረግ ላበረከታችሁት አገልግሎት የተቀበላችሁት ካሳ፣ 2. ከለጋሽ አገሮች በኢትዮጵያ ስም የሚሰበሰበው ገንዘብ፣ 3. የሀገሪቱን ጠቅላላ የገቢ ምንጮች የወርቅ፣የቡና፣ የልዩ ልዩ የርሻ ምርቶችን፣ የኢንዱስትሪ ወጠፆችን ንግዱንና ደለላወን ሁሉ በቀጥታና በተዘዋዋሪ በቁጥጥራችሁ ስር በማድረግ፣4. የኢትዮጵያ ገበሬ የሚያረሰው ቦታ እያጣ ሲንከራተት ለቻይና፣ለሕንድ፣ለሳዉዲ ለመን ሜሬት በማሻጥ እናንተ ግለሰቦቹና ፓርቲያችሁ ሚሊዮኔር ሳይሆን ቢሊያረደሮች በመሆን በአፍሪካ ምድር ተወዳዳሪ ፓርቲዎችና ግለሰቦች የሏችሁም፡ 5.ተቃዋሚዎቻችሁን ለመካላከልና ርዳታ ለማግኘት ለሱዳን ከፍተኛ ሜሬት ከአትዮጵያ ገንጥላችሁ ጉቦ ስትሰጡ ለጅቡቲም ብዙ ጋሻ የእርሻ ሜሬት ለግሳች|ል፡፡ 6.ማለዮ ለባሽ የተባለው ሰራዊት የተሰለፈው ለሀገርና ለወገን ጥበቃ ሳይሆን ሀገርን ለማሻጥ ሕዝብን ለማብታተን የተደራጀወን የወያኔን ፓርቲ ለማጠናከርና ለማገልገል ነው፡ በዚሁ ሁሉ ገንዘብ የከበራችሁ በኢትዮጵይ ዙሪያ ገብና ከሩቁም በተሰለፉባት የጠላት ኃይሎች የተደገፋችሁ ስትሆኑ ሆዱን አስርባችሁ ኖሩሉን አደንዝዛችሁ የምትገዙት ሕዝብ ወሻ ጅራቱን ቆርጦ ያበላወን ጌታወን ሥጋ ያበላው ማስሎት እንደሚከተለው ሁሉ ዙሪያው ገደል የሆነበት ከርታታ ሁሉ ለጊዜው ላንድ ሰሞን ያዘዛችሁትን ይቀበላል፡፡ ግን ዶክተር አሉላ ዋሴ «ሁሉም ያልፋል» እንዳሉት በቅርብ ጊዜ ሥልጣኑም ገንዘቡም ተንኮሉም ባንድነት ተጠቅልሉ ያልፋል ይጠፋል፡፡

አቶ ማለስ በኢትዮጵያ ላይ ቂም አሳድረህ የምትበቀላት ለምን ይሆን? መኮሎኒ እንኳን ያልተናገረወን የኢትዮጵያ ታሪክ የመቶ አመት ታሪክ ብቻ ነው ማለትህስ የትኛ ደንቆሮ የታሪክ መምህር ቢያስተምርህ ይሆን? አቶ አብርሀም ያዬ ማለስ «የኤርትራ ሕዝብ ትግል ከዬት ወዴት» በሚል አርእስት የጻፈው ነው በማለት ያሳተመው ጽሐፍ እንደሚያስረዳው የኢትዮጵያን ስም በተከሳሽነት 147 ጊዜ የጠቀስካት ሲሆን

የኤርትራን ስም በሕጋዊ ታጋይነት 472 ጊዜ መጥቀስህ የኤርትራ ማንጠል ምንያህል እንደሚያስደስትህ፣ ኢትዮጵያ ሳትበታተን በነጻነት መኖ[ ምን ያህል እንደሚያናድድህ ለማወቅ ከዚህ የበለጠ ምን ማስረጃ ይገኛል? ሥልጣን ከያዝክ በ|ላ በአወሮፓ አቆጣጠር Decembre 13 ቀን 1991 ዓ.ም. የሽግግር መንግሥት ፕሬዚዳንት ተብለህ በማስዬም ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ኤርትራ ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል የጻፍከው የልመና ደብዳቤ ሳይታወቅህ ለኤርትራ እያወቅህ ለኢትዮጵያ ያለህን ጠላትነት የሚያሳይ የጽሑፍ ሚረጋገጫ ነው፡፡ አገሬ ከአገሬ ይገንጠልልኝ ብሎ የተዋጋና የለመነ መሪ በአለም ታሪክ ወስጥ ተሰምቶም ተወግቶም አያወቅም፡፡ ማንጠልስ ለዩትኛው ወገን ጠቀመ?

ኤርትራን ካስገነጠልክ በ|ላ የፈጠራችሁትስ ጦርነት በአንድ አመት ጊዜ ወስጥ ከሁለቱም ወገን መቶ ሺህ ሕዝብ የረገፈበት ብዙ ቢሊዮን ብር የፈሰሰበት አቆርቋዥ ጦርነት አይደለምን? የትግራይን ሕዝብ ወርቅ ስትል የቀረወን ሽክላ ለማለት ሲዳዳህ የትግራይ ሕዝብ በቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጠልቶ በአንተ አይን እንዲታይ ወደፊትም እንዲገለል ለማድረግ በማጣር የዘረኝነት በሽታ በሁሉም ዘንድ እንዲዳረስ አድርገሃል፡፡ አቶ መለስ ሥልጣን ከመያዝህ በፊትና ሥልጣን ከያዝከም ጀምሮ በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ ባለፉት 30 አመታት በወር፣ በአመት ሳይሆን አንተና ቡድኖችህ እለት በእለት የምትፈጽሙት ግፍና በደል ተዘርዝሮ የሚያልቅ ስላልሆነ እዚህ ላይ አቄሜ ቀደም ሲል በወጣትነት ዘመኔ ለንጉሡ ነገሥቱ ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ቀጥሎም በጎልማሳነት ዘመኔ ለነመንግሥቱ ኃይለሚርያም ባይቀበሉተም ምክር አካፍዬ ስለነበር፣ አሁን ደግሞ ላንተም የሚበጅ ምክር ልሰጥህ እወዳለሁ፡፡

በኢትዮጵያ የጥፋት ዘመቻ በከፍተኛ ሥልጣን ሙሉ በሙሉ ካንተ ጋር ተካፋይ ከነበሩት ወስጥ ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳና አቶ ሰዬ አብርሃ ወደህሊናቸው ተመልሰው ለኢትዮጵያ አንድነት መታገል ጀምረዋል፡፡ አቶ ታምራት ላይኔም ስኳር በመላሱ ጥቂት አመታት ከታሰረ በ|ላ እግዚአብሔር ተገልጾለት መልአክ ለመሆን ወንጌልን በማስበክ ላይ ነው፡፡ በራሱና በእቁባቶቹ ስም አገር ወስጥ የነዛወና ሲዊስ ባንክ ያስቀማጠወን የኢትዮጵያ ሀብት ከማለሰ ሊቀ መላእክት ሊባል ይችል ይሆናል፡፡ ግን የመሳና ንጉሥና ንግሥት በሚዘሉት አገር እንኳንስ በእርቦ በቄናና በእንቅብ እየዛቁ እያንዳንዳቸው 40 – 50 እና 100ሚሊዮን ዶላር በመላው አለም ባንኮች ያስቀመጡት [1]ደኞቹ በሥልጣን እያሉለት ማን ደፍሮ ሊያስመልሰው ይችላል? ያስጠጋው የእምነት ድርጅት ግን የሌቦች ዋሻ በመባል እንዳየነቀፍ ማጠንቀቅ አይገባወምን?

አቶ መለስ! ሰሚን እንኳን ለመጥራት የምትጸዩፋትን አገር 19 አመት በመግዛት በሀገሪቱ ላይ እንዲደርስ የፈለግኸወን ጥፋትና ወድቀት ሁሉ ፈጽመሀል፡፡ ይህም ሆኖ ለመንግሥቱ ኃይለሚርያም ልኬለት በነበረው ምክር አይነት ራስክን አታጥል ወይም ግደል ለማለት አልደፍርም፡፡ ምክንያቱም እንደመንግሥቱ ጀግና ለማሣል «ኢትዮጵያ ወይም ሞት» «አንድ ሰው አንድ ጥይት እስኪቀር» ብለህ ስላልፎከርክና ጉዳይህም ባልሆነው የኢትዮጵያ ጉዳይ ሊከሰሁ አይገባም፡፡ ግን በሌላ በኩል የምመክርህ ትንሽ የሰወነት ተፈጥሮ ቢሰማህ፣ ትንሽ የሰወነት ሕሊና ቢተርፍህ፣ በነዚሁ ጥሪቶችህና በተፈጥሮ ጮሌነትህ እስከ ሜጨረሻው አወድሜ እወድማለሁ ከሚለው የተንኮል ተግባር ለማላገል ጥረት አድርገህ ቢቻል ቢቻል የቀረችዋን ኢትዮጵያን ለማትረፍ እንዲቻል በአገር ወስጥና በውጭ አገር ከሚገኙ ሕዝባዊ ማህበሮች ከነቃፊም ሆነ ከደጋፊ ፓለቲካ ፓርቲዎች፣ ከአርበኞች፣ ከማለዮ ለባሹ ሰራዊት፣ ከገበሬው፣ ከሰራተኛው፣ ከማህራኑ ክፍል የተወጣጣ ለአንድ አመት የሚቆይ የሽግግር መንግሥት አቋቁመህ አንተ ወርቅህንና ንብረትህን በአወሮፕላን ጭነህ እፈለግኸው አገር ሄደህ ከሚስትህ ጋር በየአገሩ ካስቀመጣችሁት ገንዘብ እየማዘዛችሁ ያለፍርሀት ያለ ቅገት ያለጭቅጭቅ እየተንፈላሰሳችሁ ትኖራላችሁ፡፡ ሱዳን ብትሔዱ፣ ሳወዲ፣ ቻይና፣ ሕንድ፣ እንግሊዝ፣አሜሪካ ያነተ ወለታ የሌለበት መንግሥት ስለሌለ ሁሉም ተቀባያችሁ ነው፡፡ እየተሰደቡ፣እየተዋረዱ፣ እየተጠሉ፣በራስ ሥራ የገዛ እስረኛ ሆኖ እየተሸማቀቁ ተደብቆ ከመኖር ራስ ነጻ አድርጎ ሕሊናን አጽድቶ እንደ እስረኛ በዘበኛ እየታጀቡ ከመኖር እንደልብ ወጥቶ በመግባት በነጻነት የመኖርን ያህል ደስታ የሚሰጥ ሌላ ነገር ያለ አይመስለኝም፡፡

አገራቸውን ወገናቸውን የሚወዱ ዘመናዊ ታላላቅ የአለም መሪዎች አራት አመት ቢበዛ ስምንት አመት ከገዙ በ|ላ በሕጎቻቸውና በፈቃደኝነት ሥልጣናቸውን ለቅቀው ይሰናበታሉ፡፡ አንተስ ዘመናዊ ነኝ ባይ አይደለህም? ለምን እንደ ድንጋይ ዘመን መሪዎች በሥልጣን ገደል ላይ ተጣበቀህና ተንጠልጥለህ መኖርን ሚጥክ፡፡ በአሁኑ ዘመን የኢትዮጵያ ሕዝብ በደርግ መጆሻ ተቀጥቅጦ በወያኔ ማጋዝ ተሰነጣጥቆ ስለተዳከመና ስለተኮላሸ «የነብር ጅራት አይዘም ከያዘም አይለቁም» እንደተሰኘው የአባቶች ተረት ሳይሆን የአሁኑ ትወልድ አብዘኛው ስለተኮላሸ ይዘው ቢለቅቁት የሚያሰጋ አይደለም፡

በደርግ ዘመን ሲቀጠቅጠት ልጆቹን በቀይ ሽብር፣ በነጭ ሽብር ሲቀጥፉበት የነበሩትን፣ እናት፣ እህትና ወንድሙን ሲያስሩ፣ ሲገርፉ ሲረሽኑ የነበሩትና የፓሊሲው ደጋፊ በመሆን ከፍተኛ ባለሥልጣን የነበሩት ሁሉ ከነዚህም ወስጥ አምልጠው አወሮፓና አሜሪካ ገንዘብ እየተሸከሙ ገብተው ስደተኞች የተባሉት ሁሉ በኢትዮጵያ ሕዝብ ደም ከብረው አገር ወስጥ በሚስቶቻቸው፣በልጆቻቸው ስም ቪላ እየሰሩ የሚያከራዩ አሜሪካ በቨርሊ ሄልስ ጭምር ቪላ የገዙ፣ በካዲላክ መኪና የሚንቀባረሩትን የቀድሞ አምባሳደሮች፣ ሚኒስትሮች፣ ጄኔራሎችና [1]ዶች አክብሮ ከመቀበል በስተቀር የአገሬ የወገኔ የቤተሰቤ ጠላት በሚለት ዞር ብሎ የሚገላምጣቸው የለም፡ ካንተም ጋር ተባባሪ በመሆን አገር በሻጥ ሕዝብን ከፋፍሎ በማባታተን በማገደልና እርስ በእርስ በማፉጀት በፐሬዚዴንትነት በጠቅላይ ሚኒስትርነት፣ በሚኒስትርነት በአገር ገዥነት ኢትዮጵያን ሲያጠፉ ቆይተው በ|ላ ዘወር ብለው የሕዝብ ወገን ከሆኑት ተቃዋሚዎች ጋር በማስለፍ ላይ የሚገኙትንም ጭምር ሕዝቡ አክብሮ ከመቀበል በስተቀር ትላንት በድላችሁኛልና ተከሰሱ ተቀጡ ብሎ ያንገራገረ የለም፡ ባይሆን የሞተው ሞቶ ቀሪው የተቸገረው፣ የተንከራተተውና ቤት ንብረት ሳይዝ በወርደት የሚኖረው ባለፉት 37 አመታት የደርግን ፋሺሽት መንግሥት አልቀበልም ብሎ ቀጥሎም ከዘረኛው ከወያኔ አልተባበርም በሚለት ለዲሞክራሲ ሲታገል የኖረው አርበኛና ስደተኛ ብቻ ነው፡

ስለዚህም አንተም ከላይ እንደተገለጸው በሚጨረሻው ሰዓት የቀረችውን ኢትዮጵያን የሚያድን እቅድ አዘጋጅተህ የመንግሥት ማሻጋገሪያ ኮሚቴ አቋቁመህ ብትፈልግ ኢትዮጵያ ከፈራህም አንድ ሌላ አገር ሄደህ አባ ጳወሎስን የነፍስ አባት አድርገህ ብትኖር ታላቅ መሪ ! ታላቅ ሰው ተብለህ ላንተም ለቤተሰብህም ጥሩ ታሪካ አትርፈህ ለዘለአለም እንደነ ቴዎድሮስ፣ እንደነ ዮሐንስ፣ እንደነ ምኒሊክና እንደነ ኃይለሥላሴ ስምህ በክብር ማዘገብ ላይ ይኖራል፡፡ ይህን ምክሬን አቃልለህ ችላ ብለህ ብትዘገይ ከመንግሥቱ ኃይለማርያም በባሰ ሁኔታ ተዋርደህ ሲሆን ሲሆን ተይዘህ በእስር ቤት ወይም እመንገድ ላይ ተቀጥቅጠህ በመሞት ወይም ፈርጥጠህ ለሚያሰጋ ስደት ሰለባ ትሆናለህ፡፡ ብታምንም ባታምንም ባለፉት 50 አመታት ስለአገሬ ጉዳይ የተናገርኩት ሁሉ ተፈጽሟል፡፡ የዛሬ አርባ አመት ያሳተምኳት አለም የተሰኘች ድርሰቴን ብታነባት ያልኩት ሁሉ መድረሱን ያስረዳህል፡፡

**<u>ሁለተኛ/</u>** አባ ጳወሎስም የምሰጠው ምክር እርስዎ በእግዚአብሔር ቢያምኑም ባያምኑም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፓትሪያክ ሆነው ከወያኔ መንግሥት ጋር ሥልጣን ይዘዋል፡፡ እግዚአብሔር ይቅር ይበለኝና ፓትሪያርኩን ቢያምኑም ባያምኑም ያሰኘኝ አንድ ታላቅ ፓትሪያርክ ሆነው እግዚአብሔር አለልኝ በሚለት ፈንታ ማለስ አለልኝ ብለዋል የሚሉ ቆሞሶችና መነኩሳት የጻፉትን ጽሁፍ በማንበቤ፣ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ወስጥ ባህታዊውን በማስገደልዎ፣ ጎንደር አደባባይ ኢየሱስና አዲስ አበባ ልደታ ማርያም ምዕመናኑን በማስገደልዎና በማስደብደብዎ፣ ከሲኖዶስ ሕግና መመሪያ ውጭ በጠምንጃ አፈሙዝ ኃይል በወያኔ ጭፍ የፓትሪያርክነቱን ሥልጣን በመቀማትዎ፣ የመነኩሴ ኃይሉና ጠብቂው እምነቱና ማስቀሉ መሆኑን ዘንግተው በኢትዮጵያ ብዙ ገዳማት ተራቁተው በሚያሳዝን ድህነት ላይ እያሉ የራስዎን አለማዊ ሕይወት ለማጠበቅ በብዙ ሚሊዮን ብር ጥይት የማነባው መኪና በመግዛትዎና በሌላ ሌላም በማሳሰለው ሁሉ ሕዝበ ክርስቲያኑን እያሰቀዬሙ ቤተክርስቲያንን ከፋፍለው ብዙ ወጣት ከእምነቱ እንዲኮበልል በሚድረግዎ በጸጸቱና በእርግጥ አማኝ ከሆኑ የሃይማኖት አባቶችንና ቀሳወስቱን ሁሉ አስታረቀው ሥልጣንዎን ለቅቀው ከአቶ ማለስ ጋር ቢ[1]ዙ ወይም ቢችሉ አንድ ገዳም ገብተው በጸለዩ እንደነ አቡነ አረጋዊ እንድ አቡነ ተክለኃይማኖት እወነተኛ ቅዱስ ተብለው ሊጠሩ ይችላሉ፡፡ ገዳም

ከገቡ እኔም እግዚአብሔር እድሜ ከሰጠኝ እዘጉበት ገዳም ድረስ መጥቼ ይቅርታ በማጠዬቅ ማስቀልዎን እሳለማለሁ፡፡

**<u>ሶስተኛ/</u>** የቀራችሁት አድር ባዮችና ሆድ አደሮች የወያኔ ቅጥረኞችና ተባባሪዎች በመሆን የምትፍጨረጨሩ ሐቀኛ ሰራተኞችና ታታሪዎች 20 እና 30 አመት ለፍተው ጥረው ገረው ሊያከማቹት ያልቻሉትን ሀበት ከወያኔ ባለሥልጣኖች ጋር በመተባበር በኮንትሮቫንድ፣ ለሕዝብ የሚያስፈልገውን ገንዘብና እርዳታ በማዘረፍ የንግድ፣የእንዱስትሪና ልዩ ልዩ የምርት ወጠፆችን ከወያኔ ጋር በሽርክና በግል ቁጥጥራችሁ ስር አወላችሁና በሞኖፖል ይዛችሁ አገሪቱንና ሕዝቡን በማብዝበዝ በአጭር ጊዜ ወስጥ ሚሊዮኔር የሆናችሁ የፍርድ ቀን ስለቀረበች ወዮላችሁ፡፡

**/የዛሬ 40 አመት «አለም» በተሰኘችው አነስተኛ መጽሐፌ «ዘራፍ ማስፍንቶች ማስፈናችሁ ቀረ ዘራፍ መኳንቶች ማዘረፋችሁ ቀረ ሲዘረፍ የነበር ሕዝብ ተባበረ በማበር ፈንታ ሚሊዮአስገበረ፣ ሲናቅ የነበረው ዛሬ ተከበረ፣ ይኼ ያለማቱት ሕልም የሀሳብ ትንቢት ቢወልና ቢያድር ቢቆይም ጥቂት መድረሱ እማይቀር ነው አትጠርጥሩት/ገጽ 36/»ብዬ በጻፍኩ በአራተኛው አመት የደረሰወን ማስተዋል በቂ ነው፡፡/**

**ነገር ግን ለኃጥአን የመጣ ለጻድቃን ይተርፋል እንደተባለው በጥቂት ተንደላቃቂዎች ምክንያት ሰርቶ ለፍቶ በንጹህ ላቡ ሀብትና ንብረት የነበረው ሁሉ አድሀሪ በማባል ንብረቱን ተቀምቶ መሳሪያ ታጣቂ ለሆኑ ወሮበላ ወታደሮችና ለግብረ አበሮቻቸው ሚፈንጠዛና ጠማኝ መግዣ ሆኖ መቅረቱ ነው፡፡**

**በዛቺው መጽሐፌ በገጽ 24 እንደገለጽኩት «ሰባቂ አጫብርባሪ ባለጌ ይጠበቅ፣ ግፈኛው ጉረኛው ቀማኛው ይታወቅ፣ አድርባዩ ግብርአበር በብረቱ ይጠንቀቅ፣ መኛ አረሙ ሁሉ ተነቃቅሎ ይወደቅ፣ ትልቅ ትንሽ ሳይል እረጅም አጭር፣ የእወነት ደበኛ የዲያቢሎስ ዘር፣ ይታሰር ይወገር ይጥፋ ይመንጠር፣ የሚል ነበር፡፡**

**አሁንም የሚማጠሩበት ቀን ስለተቃረበ የፍርድ ቀን ከመድረሱ በፊት ወያኔን ከዳችሁ የዘረፋችሁትን ንብረት ለሕዝብ አስረክባችሁ ከሕዝብና ከሕሊናችሁ ብትታረቁ ራሳችሁን ከሚጨረሻው ወድቀት ታድናላችሁ፡፡**

**እርግጥ «ተከተል አለቃህን ተሜልከት አላማህን» እንደተባለው እንዳንድ አድር ባዮች ለአራት መንግሥታት የሰሩትን በ4 መንግሥት የተሾሙትን የተሸለሙትን የከበሩትን ፕሬዚዳንት የመቶ አለቃ ግርማን ችሎታ በሚድነቅ አላማችን የብልሆች ጥበብ ነው ሊሉ ይችላሉ፡፡ ግን አያዋጣም የፍርድ ቀን እየቀረበች ነው፡፡**

**<u>አራተኛ</u>** በሌላ በኩል ወያኔን እንቃወማለን የሚሉ ብዙ የፖለቲካና የትግል ድርጅቶች መኖራቸው ይታወቃል፡፡ እዚህ ላይ ጥያቄው ተቃዋሚዎቹ በእወነት ለአገርና ለወገን ተቆርቁረው ኢትዮጵያን ከጥፋትና ከወድቀት ለማዳን ይሆን? ወይስ እኛስ ከማን አንሰን ለኛም የሥልጣን ተራ ይድረሰን በሚል ይሆን? በየጎሳው፣በየጎጡ፥በየመንደሩና በየሰፈሩ ስም የፖለቲካ ፓርቲ የሚያቋቁሙት ተቃዋሚዎች የወያኔና የሻቢያ የሚጨረሻ አላማና ግብ ፈጻሚዎች ቢባሉ ይቀላል፡፡ እወነተኛ ፖለቲከኞች ከሆኑ ከ50 እስከ 60 እና 100 ፓርቲዎች ማቋቋሙ የምን ፈሊጥ ይሆን? ሁሉም የዲሞክራሲ መንግሥት ለማቋቋም እንታገላለን ባዮች ናቸው፣ ግን እኮ መጀመሪያ የዲሞክራሲን ጽንስ ሃሳብ የነደፉት ግሪካወያኑ እን አርስቶትል እነ ሶክራትስ እነ ፕላቶ ያቀረቡትን ሐሳብ ብንሚምር ዲሞክራሲ ብዙዎች ተነጋግረወበት አብዛኛው ድምጽ የደገፈው ኃሳብ አሸናፊ መሆኑን ከመግለጹ በስተቀር ብዙ የፖለቲካ ፓርቲዎች መቋቋም አለባቸው የሚል አስተያዬት አይገኝበትም፡፡ የዲሞክራሲ ጽንሰ ሃሳብ ተነድፎ በተግባር ላይ ሳይወል ከሁለት ሺህ አመት በላይ ካለፈ በ|ላ በዲሞክራሲ ስርአት የተሚረጠ የሕዝባዊ መንግሥታት አሜራርን ለመጀመሪያ ጊዜ ተግባራዊ ሚድረግ የጀመሩት አሜሪካና ፈረንሳይ ናቸው፡፡ በተከታታይም የምዕራብ

አወሮፓ መንግሥታትም በዚሁ ስርአት እየተጠቀሙበት ነው፡፡ የእነዚህ ዲሞክራሲያወያን መንግሥታት ሕዝብ በሁለት ወይም በሶስት ዋና ዋና ፓርቲዎች ተደራጅቶ የሚወዳደር ሲሆን በተጨማሪም አፈንጋጮችን የሚያሰባስቡ ወይም ቀድሞ ያልነበሩ አዳዲስ ሃሳቦችን የሚያንሸራሽሩና የዋናዎቹን ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ሚዛን በሕዝባዊ ስሜቱ የሚያስተካክሉ ቢበዛ አራትና አምስት ፓርቲዎች በጎን ለወድድር ከመቅረባቸው በስተቀር እንደኛ ከማን አንሼ በሚል 50-60 -100 ፓርቲዎችን በመፍጠር ወይም የአንድ ፓርቲ ፕሬዚዳንት ከተባላን አሸንፎ ሥልጣን የሚከበው ቡድን ለማበያ አንድ ቦታ ይሰጠንና እንጠቀማለን በማለት አያወናብዱም፡፡ ሰፈሩን፣መንደሩን፣ጎጡን፣ዘሩን፣ ሃይማኖቱን፣ቋንቋወን ወዘተ ሰበብ በማድረግ በፓርቲ ስም የሚ[ጡ ብልጣብልጦች ሁሉ ለሕዝብ ያሰቡ በማምሰል ሕዝብን የሚያሳፍኑ ዲሞክራሲያዊ ማስሎ በሚታለል ዲሞክራሲን አስረው ለአምባ ገነናዊ ስርአት በምልጃነት እጅ መንሻ የሚያቀርቡ ፀረ ሕዝብና ጸረ ዲሞክራሲ ቡድኖች ናቸው፡፡

አሁን በኢትዮጳያ ሥልጣን የያዘው መንግሥት እንደ ወራሪ፣ እንደቅኝ ገዥ የሚቆጥር የኢትዮጵያ ጠለቶች መሳሪያ በመሆኑ በፓለቲካ በኩል መቶ ፓርቲዎች አቋቁሞ በማብታተን የሚቋቋመት ሃይል ስላልሆነ ከሱ ብጤ ዘረኞችና ጎጠኞች ጋር መተባበር ባይቻልም ለአንድነት የቆመት ሁል ከሥልጣን ሺሚያ ተቆጥበው በመጀመሪያ አገርን ለማዳን የሚያስችል አንድ ማለስተኛ የጋራ ፕሮግራም በማውጣት ቢታገሉ ኢትዮጵያን ማዳን ይቻላል፡፡ በሁለ ገብ ትግል እንታገላለን የሚሉ ድርጅቶችም ልዩነቶችን አስወግደው በአንድ የጋራ መመሪያ ተደራጅተው ከታገሉ የወያኔን እድሜ ማሳጠር ይችላሉ፡፡ ይህ አስካልሆነ ድረስ ወጡቱ ወሃ ቢወቅጡት እንቡጭ እንደተባለው ነው፡፡ በእርግጥ አንድነት ተማስርቶ ህጋዊ ዲሞክራሲያዊ ሕዝባዊ መንግሥት እንዳይማሰረት ለማድረግ ከሥልጣን ሽሚያው ሌላና ከወያኔ ሻጥርም ባሸገር እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል በሚል ሜልክ በአሉባልታ ብቻ የሰለጡ በተለይ በአገር ወዳድነትና በእንከን የለሽነት የሚታገሉ አርበኞችን ስም በሀሰት በማጥፋት ሁሉን ከሁሉ በማጣለት የታወቁ ጠንቀኛ ፓራሳይቶች ስላሉ ከነሱ ማጠንቀቅ አስፈላጊ ነው፡፡

**<u>አምስተኛ</u>**/የኢትዮጵያ ማለዮ ለባሽ ሰራዊት አቋምስ እንዴት ነው? ወታደር የአንድ ግለሰብ ወይም የአንድ ቡድን አሽከር በማሆን ዳር ድንበሩንና ማህል አገሩን ለሚሸጥ፣ሕዝቡን ከፋፍሎ ለሚበታትን አሳፋሪ አሚራር መሳሪያ ሆኖ የሚያገለግል ከሆነ የሚፈያ ቅጥረኛ ሆድአደር እንጅ አገርና ወገኑን የሚጠበቅ ወታደር ሊባል አይችልም፡፡ የዛሬ 30 አመት ገደማ እኔና የትግል [1]ደኞቼ ሱዳን ምድር ሆነን በእምዱሩማን ሬዲዮ ጣቢያ ባለሰተላለፍነው የሬዲዮ ሜእክትና በአገር ወስጥም በበተበነው ጽሑፍ ከዚህ በላይ ያሰፈርኩትን በመመዝገብ የኢትዮጵያ ማለዮ ለባሽ ሰራዊት የደርግ ልዩ አገልጋይነቱን አቋርጦ ከሕዝብ ወገን እንዲሰለፍ በሚደጋግም አሳስበን ነበረ፣ ምክራችንን ሳይቀበል ከቆዬ ግን የ|ላ|ላ አፍሮና ተዋርዶ ለልመናና ለዘረፋ ወንጀል እንደሚጋለጥ አስጠንቅቀነው ነበር፣ ምክር ባለመቀበሉ ደርግ ሲፈርስ ማለዮወንና ሜዳሊያወን እመንገድ ላይ እያነጠፈ ሲለምን ከረሙ፡፡ ከፊሉም በ19991 ዓ.ም. ወያኔና ሻቢያ ባደረጉት የቲያትር ጦርነት ወደሥራው ተሜለሶ በመቀጠር ባድሜ ዛል አነበሳ ላይ እንደ ቅጠል ረገፈ ፡፡ ይህ እንዳይደርስበት ቀድመን ነግረነው ነበር፡፡ አሁንም ለወያኔ ማለዮ ለባሽ ሠራዊት የማስስበው ራሱን ከወያኔ አሽከርነት ነጻ በማውጣት ወያኔን አስወግዶ የአገርና የወገን አገልጋይ በማሆን ራሱን ከወርደትና ከወድቀት ለማዳን እንዲሸቀዳደም ነው፡፡

**<u>ስድስተኛ/</u>**የኢትዮጵያ ሕዝብስ በአሁኑ ጊዜ ከምን ደረጃ ላይ ይገኛል? ኢትዮጵያ /የኢትዮጵያ ሕዝብ/ በተለይ ከ5ኛው ምዕተ አመት እስከ 7ኛው ምዕተ አመት በነበረው ጊዜ ወስጥ በኢኮኖሚ እድገት፣ በካልቸር ጥራት፣ በወታደራዊ ኃይልና በመንግሥታዊ አሚራር በዘሙኑ በአለም ላይ ከነበሩት አራት ታላላቅ መንግሥታት አንዷ እንደነበረች በአለም ታሪክ የተረጋገጠ ነው፡ ግን በተለይ ከ10ኛው ምዕተ አመት ጀምሮ ብዙ ጊዜ አዘቅት እየወረደች አልፎ አልፎም ራሷን ቀና እያደረገች ጠፍታ ሳትጠፋ፣ ለምታም ሳትለሙ፣ በብቅ ጥልቅ ለአንድ ሺ አመታት ቆይታለች፡፡ ሆኖም ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ወርራ ከተባረረችበት ከ1933 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1960 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ ወስጥ ኢትዮጵያ ከፍተኛ እምርታ ያስማዝገበችበት ጊዜ ነበረ፣ ከዚያን በ|ላ በተለይም ከ1966 ዓ.ም. ጀምሮ ባልተጠና

ጥንቃቄ በጎደለው ለወጥ በተሰኘ ትርምስ ቀደም ሲል በጥቂት ደንቆሮ ወታደሮች አሜሪር ቀጥሎም ተንኮልን በተካኑ ዘረኞችና ጎጠኞች ቡድን የአገዛዝ ስልት ሕዝቡ ተሸብሮ በስድብ፣ በድብደባ፣ በእስራት፣ በግርፋት፣ ቤት ንብረቱን በመቀማት፣ የተገደለው ተገድሎ የቀረው በማስደድ ወይም ተዋርዶ በአገር ወስጥ በማንከራተት፣ ማስቢያ ሕሊናው አስተዋይ ልቡናው ተጎድቶ ሞራሉ ዝቅ ብሏል፡፡ የሁለቱ ተከታታይ መንግሥታት ፓለቲካ አሉባልታና ሀሰት በመሆኑ በነዚህ መንግሥታት ያደጉ ሁሉ ብዙ መጥፎ ጠባይ ይጋባባቸዋል፡፡ በሀሰት ታሪክም ይታነጻሉ፣ በማላያዬትና በጥላቻም ይሚዛሉ፡፡ ሳያወቁትም ለሀገራቸው፣ ለወገናቸውና ለራሳቸውም ጠላት ሆነው እንዲኖሩ ይቀረጻሉ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ አይነት ወጥመድ ወስጥ መሆኑን ተረድቶ ወጥመዱን ለማብጣጠስ ማሳት አለበት፡፡ ጥቂቶች የመንግሥት አባላት፣ ተባባሪዎች፣ደጋፊዎች፣ ሚኒኔሮች፣ ባለቪላዎች፣ ባለሕንጻዎች፣ ባለሚርቼዲስና ባለሬንጅሮቨር ሚኪናዎች ሆነው ሲንደላቀቁ ከመቶ ሰማንያው እጅ ሕዝብ የሚጠጣው ንጹህ ውሃ፣የሚማበው በቂ ምግብ፣ የሜኖርበት በቂ ቤት፣ የሚታከምበት ገንዘብ የሚለብሰውና የሚያደርገው ጫማ ሳይኖረው በችግርና በበሽታ እንዲሰቃይ ያደረገወን ሥርአት ደምስሶ የእድገትና የሜልካም ኑሮ አሜሪር እንዲተካ ለሚድረግ ሁሉም ሕዝብ ባንድነት ማሳት አለበት፡፡

ኢትዮጵያዊ ሁሉ አገሩ የኢትዮጵያ የወስጥ ጠላቶቿ እንምብርቷ ላይ ቆመው እየረገጡ የሚያሰቃዩዋት መሆኑን ተረድቶ፣ በልዩ ልዩ ምክንያት በዙሪያ ገብ ጠላቶች የተከበበችና ከሩቅም ወድቀቷን በሚመኙ ምቀኞች የምትጠቃ መሆኑን ተገንዝቦ ከዚህ ሁሉ አደጋ ለሜከላከል አንድ ከዘር ከሀይማኖትና ከፖለቲካ ወቨንብር የራቀ **<u>አለም አቀፍ የኢትዮጵያወያን አንድነት ማህበር</u>** ሚቋቋም የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህንንም ማህበር ለሚቋቋም በሜላው ኢትዮጵያ በየሰፈሩ፣በየቀበሌው፣በየወረዳው፣በየአወራጃውና በየክፍለሀገሩ የሚገኙ የሀገር ሽማግሌዎች ልዩ ልዩ የሕዝብ ማህበራትና እድሮች በጀርባ አጥንትነት ማስለፍ ይገባቸዋል፡፡ ማህበሩ ሲደራጅ በስመ ዲሞክራሲ ዲሞክራሲን ለማብታተን በመንግሥት ድጋፍ በየመንደሩ የሚቋቋሙ ወይም ከማን አንሼ በሚል ለጉራ ወይም ለጥቅም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የትግል ድርጅት አቋቁማለሁ በማለት የሚፈነጩዋን ሁሉ በመግታት ማህበሩ ለአገሪቱ አገልግሎት ሊሰጡ የሚቹሉ በእወነተኛ ቁም ነገር ላይ የሚማሰረቱ ሁለት ወይም ሶስት ፓርቲዎች ተቋቁመው የሚወዳደሩበትን ሥርአት በመመሥረት የኢትዮጵያ አንድነት. ሰላምና እድገት የሜፉጠንበትን መንገድ ይደለድላል፡፡

ይህ ማህበር የኢትዮጵያ እድል የሚቃናበትን መንገድ ከመደልደልና ከሚቃናት በስተቀር እራሱ የፓለቲካ ፓርቲ አቋቁሞ ለመወዳደር ወይም ለአንድ የተለዬ ፓርቲ ድጋፍ የሚሰጥ ማህበር ሊሆን አይገባወም፡፡ ስለማህበሩ አሰራርና ሀሳብ አጭር ንደፍ ኢትዮጵያና እድሏ በተሰኘው መጽሐፌ ከገጽ 230-234 መሜልከት ይቻላል፡፡ ኢትዮጵያን ለማዳን ኢትዮጵያዊነን የምንል ሁሉ የተጣላን እንኳን ብንኖር ይቅር ተባብለን እጅ ለእጅ በማያያዝ ካልተነሳን በስተቀር እኔ እበልጥ! እኔ እበልጥ ያ እንዲህ ነበር ይህ እንዲህ ነው በማለት በየፊናው የሚደረገው መፍጨርጨር ወጤት አልባ ነው፡፡

ስለዚህ ኢትዮጵያወያን ተወያይተን ተደማምጠን ብንሰራ ራሳችን ድነን አገራችንን እናድናለን፡፡ እያንዳንዱ ራሱን በማበለጥለጥ ሌላወን እየናቀ ቢያልፈው እያንዳንዱ ተንቆ ይቀራልና እንደማመጥ፡፡

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን

ከክፉ አወሬ እንዲገላግላት በሜጸለይ እንታገል፡፡

ኮሎኔል አሥራት ቦጋለ